Amharic

# ልጄ የሁለተኛ ዓመት ምውአለ ህጻን ያስፈልገዋልን?



ህጻናት ት/ቤት ለመጀመር አንድ ዓመት ሲቀራቸው ወደ ምውአለ ህጻን እንዲሄዱ በቪክቶሪያ መንግሥት በኩል የገንዘብ እርዳታ ይቀርባል።

ህጻናት ለመማር ዝግጁ በሚሆኑበት ጊዜ በመደበኛ ት/ቤት ውስጥ ማስመዝገቡ አስፈላጊ ነው። ስለዚህ ህጻናት ወደ ምውአለ ህጻን የሚሄዱበትን ትክክለኛው ጊዜ በወላጆች እንደሚወሰን ሁሉ - እንዲሁም ወላጆች ልጃቸውን ት/ቤት ለማስጀመር ትክክለኛውን ጊዜ ግምት ውስጥ ማስገባቱ አስፈላጊ ነው።

አንድ ህጻን ቢያንስ በሁለት መንገድ የእድገት ዝግመት እንዳለበት በአስተማሪ በኩል ተጣርቶ ከታወቀ እና እሱ/እሷ ሁለተኛውን ዓመት በምውአለ ህጻናት ላይ በመሳተፍ ጥቅም ካገኘ/ች ይፈቀድለታል/ላታል ማለት ነው። በእድገት ግምገማ ላይ መካተት የሚችሉት እንደ እራስን መንከባከብ፣ ቋንቋን የመናገርና/ወይም የመረዳት ችሎታ፣ የግንዛቤ (የአእምሮ ትምህርት) መሻሻል፣ የማህበራዊ እድገት እና ስሜታዊ ስለመሆን እድገት ናቸው። እንዲሁም ሌሎች ነገሮችም ግምት ውስጥ መግባት ይኖርባቸዋል።

ለወላጆችና አስተማሪዎች የልጆችን ፍላጎት ለመለየትና ለነሱ የሚስማማ እቅድ ለማውጣት እንዲችሉ የሚረዳ የተለየ መመሪያዎች አሉ። በዚህ ሁኔታ ላይ ወላጅና አስተማሪ በቅርበት አብረው እንዲሠሩና በግልጽ መነጋገር ያስፈልጋል። በወላጅ ስምምነት ሲደረግና፣ ከወላጅ ጋር መማክርት ሲደረግ፣ መጀመሪያ በአስተማሪው ግምገማ ይጠናቀቅና፣ ከዚያ የቅድመ ህጻንነት እድገት ባለሙያዎች (ለምሳሌ፣ የቅድመ-ት/ቤት የሙያ ኃላፊዎች) እርዳታ እንዲያደርጉ ከተፈለገ ከዚያ የህጋዊ መግለጫ ሰነድ በመስተዳድር ክልል መምሪያ ጽ/ቤት ተቀባይነት እንዲያገኝ መላክ ይሆናል።

## ያስተውሉ

- ልጅዎ በምውአለ ህጻን መቸ መለማመድ እንዳለበት በጥንቃቄ ማሰብና ትክክለኛ ጊዜን መለየት ይሆናል። እርግጠኛ ካልሆኑ ልጅዎን ለሚያውቁ ሌሎች ሰዎችና ጥሩ ግምት ይሰጣሉ ብለው ለሚያምኗቸው ሰዎች ማነጋገር።
- ወደ ምውአለ ህጻን በመሄድ ወይም በመረጃ አቅርቦት ትምህርት ላይ በመገኘት ስለምውአለ ህጻን ፕሮግራም መጠየቅ።
- ልጅዎ የምውአለ ህጻን ፕሮግራም ከመጀመሩ/ሯ በፊትና በኋላ ስለልጅዎ ያለዎትን ሃሳብና አሳሳቢ ጉዳይ በግልጽ ከአስተማሪ ጋር መነጋገር።
- ልጅዎ በምውአለ ህጻን ለመግባት ስለትክክለኛ ጊዜ በተመለከተ በበለጠ ማብራሪያ ወይም መረጃ ለማግኘት ከፈለጉ ለህጻኑ አስተማሪ፣ ለህጻን እንክብካቤ አስተባባሪ ወይም ለእናቶችና ህጻን ጤና ጠባቂ ነርስ ያነጋግሩ።

በቪክቶሪያ መንግሥት አነሳሽነት የተጀመረ

Victoria The Place To Be

© የትምህርትና የመጀመሪያ የልጅነት ጊዜ እድገት መምሪያ፣ 2007 ዓ.ም